

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከዲሴምበር 1-10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

# እንዲሁም

# ከዲሴምበር 11-20/2025 እና ከዲሴምበር 21-31/2025

# የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


## 1. እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

በዲሴምበር የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም የሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ነበራቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከዕለት ወደ ዕለት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ጨምሮ የተስተዋለ ሲሆን በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም ሐሮማያ 3.2፣ 2.0፣ 2.6፣ 4.0፣ 4.4፣ 4.0፣ አለም ከተማ 3.2፣ 4.5፣ 4.8፣ 4.2. 4.2፣ 4.8፣ 4.2፣ አምባ ማሪያም 4.2፣ 4.5፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.6፣ አርሲ ሮቤ 2.5፣ 2.5፣ 3.0፣ 4.5፣ 4.5፣ ባቲ 3.4፣ 3.6፣ 4.0፣ 4.6፣ ቡሂ 3.4፣ 2.0፣ 2.2፣ 3.6፣ 4.0፣ 3.8፣ ጨፌ ዶንሳ 4.0፣ ጨለንቆ 2.3፣ -1.0፣ 1.8፣ 2.4፣ -1.0፣ -1.0፣ -1.0፣ 2.1፣ -2.0፣ 1.8፣ ደብረ ብርሃን 3.8፣ 3.0፣ 4.6፣ 4.2፣ 4.0፣ 4.8፣ ቢሾፍቱ 3.8፣ 3.0፣ 4.6፣ 4.2፣ 4.0፣ 4.8፣ ጋሸና 4.2፣ 4.4፣ 3.0፣ 2.4፣ ሂርና 2.0፣ 2.6፣ 4.0፣ 4.4፣ 4.0፣ እምድብር 4.8፣ ጅግጅጋ 3.0፣ 2.5፣ ኮረም 1.0፣ 2.0፣ 2.5፣ 3.0፣ 3.0፣ 2.0፣ ቁሉቢ 4.3፣ 4.5፣ 4.1፣ 3.5፣ 3.2፣ 3.4፣ 3.4፣ 4.0፣ ቁሉምሳ 4.2፣ መሃል ሜዳ 4.8፣ 3.2፣ ሮቤ 4.2፣ 3.4፣ 3.8፣ 4.8፣ እንዲሁም ወግል ጤና 2.5፣ 4.2፣ 4.8 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1)፡፡




ምስል 1፡ ከዲሴምበር 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የተመዘገበባቸዉ ስፍራዎች

በሌላ በኩል በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ገጽታ ነበራቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት ጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ5 ሚ.ሜ በላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ሮቤ 6.7፣ ቻግኒ 5.4፣ ጨዋቃ 7.2፣ ጋቲራ 5.9፣ ጊምቢ 16.2፣ ቁሉምሳ 5.3፣ ማሻ 5.6፣ ቴፒ 11.7፣ 16.2፣ አሺ 7.8፣ ቢላምቢሎ 6.5፣ እንዲሁም ሼንዲ 6.5፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ቀላል መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በአስራ አንድ (11) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ5 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ቀላል መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 2)፡፡





ምስል፡2 ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ5 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ጥቂት የቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የዳዋ እና ሊበን ዞኖች ላይ ከ2-8 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

በሌላ በኩል የደቡብ ጎንደር፣ የሰሜንና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ዞኖች፤ የመተከል፣ ካማሺ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጥቀቲ የምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ ዞን፣ ላይ ከ2-31 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ከ1-4 ቀናት ያህል ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ በታች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር

Ethiopian Meteorology Institute

## 1.2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት የዲሴምበር የመጀመሪያው አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለው የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላም በኩል በጥቂት የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ ነበረው። በሌላ በኩል ከደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ የነበረው ቅዝቃዜ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች ጤናማ ዕድገት ላይ መጠነኛ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4) ፡ ፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው። ከዚህም ጋር ተያይዞ አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ተከዜ እና አይሻ ተፋሰሶች በአብዛኛው ደረቅ ሁኔታዎች ውስጥ እንደቆዩ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በአንጻሩ ግን በጥቂት የላይኛው ባሮ አኮቦ እና በጥቂት የታችኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ነበራቸው (ካርታ 5)።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute

## 2. መግቢያ


በመደበኛ ሁኔታ በዲሴምበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚገባው ደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅ፣ መካከለኛው እና ደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አንጻዊ ጥንካሬ ይኖረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ውርጭ የማስከተል ጥንካሬ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡


## 2.1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የዲሴምበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በጥቂት የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናቶች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፤ ሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በመሆኑም በደቡብ ኦሮሚያ የሚገኙ የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ እንዲሁም የዳዋ፣ ሊበን እና አፍዴር ዞኖች ላይ የሚገኝዉን አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ በአግባቡ በመሰብሰብ ሊኖር የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ መቀነስ ያስፈልጋል (ካርታ 6)፡፡

በሌላ በኩል ከሚኖረው የደመና ሽፋን ላይ በመነሳት በጥቂት የደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ በሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፤የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋ፤ የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሊባቦር፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ ምዕራብ ሀረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬ ደዋ፣ የሲቲና ፋፋን ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡

Ethiopian Meteorology Institute




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ


ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 11-20, 2025 የሚኖረዉ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጥቂት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን እና አፍዴር ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

| በጥቂት አከባበቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች | | |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | የምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን፤ ምዕራብ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አማራ | ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ዋግ ህምራ ዞን እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጥቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌዲዮ፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| | አዲስ አበባ | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

በሚቀጥሉት የዲሴምብር ሁለተኛዉ አስር ቀናት ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ አየር እንደሚቀጥል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን፣ ምስራቅ፣ መከከለኛዉና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ምስል 3)።




ምስል፡3 ከዲሴምበር 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከሶስት (3) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የሚመዘገብባቸው ስፍራዎች

## 2.2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት የዲሴምብር ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ አየር እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን፣ ምስራቅ፣ መከከለኛዉና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ፣ በመካከለኛዉ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

በሌላ በኩል በጸሀይ ኃይል ታግዘው የሚፈጠሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አሮሚያ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና ጥቂት የደቡብ ሶለማሌ ዞኖች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 2.3 እ.አ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ፣ የሰብል ስብሳባ እና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት እየተከናወነ በሚገኝባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ይጠበቃል፡፡ በአንጻሩ ግን በተወሰኑ የመኸር አብቃይ በሆኑት ክልል ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በጥቂት የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ መተግበር ያስፈልጋል።

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች ዳዋ፣ ሊበን እና አፍዴር ዞኖች ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ቦሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት<br>• ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን<br>• ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የእንስሳት መኖ ከሰብል ተረፈ ምርት ማሰባሰብ እና ማከማቸት |
| **ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚጠበቅባቸው የመኸር ሰብል አምራች ዞኖች** | | | | |
| የምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን፤ ምዕራብ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ዋግ ህምራ ዞን እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች የካማሺ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ በጥቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌዲዮ ዞኖች እና አዲስ አበባ፤ | ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የጥራጥሬ ሰብሎች እድገት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት<br>• የውርጭ ስጋት መቀነስ | • የደረሱ ሰብሎች ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ መጠነኛ አሉታዊ ተጽዕኖ<br>• ከእርጥበትና ሙቀት ጋ ተያይዞ የዋግ በሽታ ስጋት መኖር<br>• በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመረ | • የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል<br>• በደጋና በውይን አደጋ አካባቢ የሰብል በሽታ ክትትል ማድረግ<br>• የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን<br>• አልፎ አልፎ የውርጭ ክስተት በሚጠበቅባቸው አንዳንድ አካባቢዎች በሰብሎችና በመስኖ በሚበቅሉ አዝዕርቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ |

## 2.4 እ.አ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት ዲሴምበር ሁለተኛ አስር ቀናት በጥቂት ተፋሰሶች መጠነኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን የተቀሩት በአብዛኛው ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የቀረቡትን ተፋሰስ ተኮር የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም አሉታዊ ተፅኖዎች እንዲቀንሱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በላይኛ ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ጥቂት በመካከለኛ እና ታችኛው አባይ፣ በመካከለኛ ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት ላይኛው አዋሽ እንዲሁም በላይኛው ገናሌ ዳዋ | መካከለኛ የእርጥበት መጠን | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም ለመጠጥ ውሀ መጠነኛ የውሀ አቅርቦት መኖር | • አንጻራዊ የትነት መጨመር | • ውሀን በተገቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የሚገኘውን ውሀ ከብክነት እና ከብክለት መጠበቅ |
| በአብዛኛው አባይ፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን እና አይሻ፣ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • ወንዞች እና ሌሎች የውሀ አካለት በደራሽ ቆሻሻ አለመበከል | • የወንዞች የዉሀ መጠን ሊቀንስ ይችላል | • የዝናብ ውሀ ከጣራ እና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |